# በኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ላይ የታወጀ ስልታዊ ጦርነት

**በአለማየሁ ገ/ማርያም (ፕ/ር)**

ቢራቢሮን ለመደፍጠጥ፣ መረጃ ተጠቀም! ያ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኘው ነፃ ፕሬስ ላይ አምባገነናዊው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያወጀው አጠቃላይ የጦርነት ስልት ነው:: በቅርብ መለስ ዜናዊ በእውነት ላይ ባወጀው ጦርነት የ'ሳት 'ራት ከመሆን ለጥቂት የተረፉ ጋዜጠኞች አገር ለቀው ጠፍተዋል:: የድረሱልን ጥሪያቸው በመላ የመረጃ መረቦች በቅብብሎሽ ተሰራጭቷል:: በጋዜጣዊ መግለጫቸው እንደገለፁት፣ «የመንግስትን ሕጋዊና ፖለቲካዊ ማስፈራሪያና ዛቻ ተከትሎ አዲስ ነገር አሳታሚ ዋና የሕትመት ውጤት የሆነችው አዲስ ነገር ጋዜጣ ስርጭቷ ቆሟል:: ቅዳሜ 28/2009 ዓ.ም የጋዜጣዋ የመጨረሻ ሕትመት ነበር::» በዚህ የስደት ማዕበል አገር ለቀው የተሰደዱት ጋዜጠኞች:- ታምራት ነገራ - ዋና አዘጋጅ፤ አብይ ተ/ማርያም - መጋቢ ኤዲተር፤ ግርማ ተስፋው - ምክትል ዋና አዘጋጅ፤ ማስረሻ ማሞ - አዘጋጅ፤ መስፍን ነጋሽ - መራሄ ኤዲተር፤ ዘሪሁን ተስፋዬ - ከፍተኛ ሪፖርተር፤ እና አብርሃም በግዜው - የዜና ሪፖርተር - ናቸው::

መስፍን ነጋሽ፣ በጋዜጣዋ መዘጋት የሥራ ባልደረቦቹ የተሰማቸው ጥልቅ ብስጭትና ሀዘን የሚጋራው ነው፤ ቢሆንም ግን በእምቢተኝነቱ ኩራት ይሰማዋል:- «ጋዜጣችን ገደቦች ሳይኖሩ በነፃነት ለመስራት ውስጣዊ ብቃት ያላቸው ገለልተኛ ጋዜጠኞች የሕዝብ አስተያየት መቀበያና ማስተናገጃ መድረክ በመሆን ምን መቀዳጀት እንደሚቻል ያሳየችና በኢትዮጵያ ውስጥ ምሳሌ ከሚሆኑ ምርጥ የሕትመት ውጤቶች አንዷ ነበረች:: እንደአለመታደል ሆኖ፣ መንግስት ሥራችንን ማከናወን የማንችልበት ደረጃ ላይ አድርሶናል» ብሏል::

በኢትዮጵያ ውስጥ በገለልተኛው ፕሬስ ላይ የሚሰነዘረው ጥቃት አዲስ አይደለም:: ከግንቦት 97 ምርጫዎች አንስቶ በገለልተኛ ጋዜጦች፣ አዘጋጆች፣ አሳታሚዎች እና ሪፖርተሮች ላይ እየተሰነዘረ በሚገኘው ጥቃት የቅርብ ተጠቂዋ አዲስ ነገር ነች:: በአምባገነኑ በርካታ ጋዜጦች ታግደዋል፤ በርካታ ጋዜጠኞች በቁጥጥር ስር ውለዋል፤ ለእስር ተዳርገዋል:: በተደጋጋሚ ካለተጨባጭ ምክንያት በፖሊስ ምርመራ ስር ሆነዋል፣ የጣት አሻራ እንዲነሱ፣ ማስተባበያ እንዲሰጡ ተገደዋል እንዲሁም ከጥብቅ ማስጠንቀቂያ ጋር የወንጀል ክስ ሳይመሰረትባቸው ከእስር ተለቀዋል:: በቅርብ የአዲስ ነገር ሪፖርተሮች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ዙሪያ ዘገባ በመስራታቸው «የፓትሪያርኩንመልካም ስም በማጉደፍ» ወንጀል ተከሰው ነበር:: ከብሔር ጋር የተያያዘ ሪፖርት በመዘገቡ ለእስር የተዳረገ ጋዜጠኛም ነበር:: በአንድ የፍ/ቤት ጉዳይ ዘገባ ላይ

የዳኛውን ስም ፊደላት የገደፈ ጋዜጠኛ እስር ቤት ለመግባት ተገዷል። በዲያስፖራ የሚገኙና የኢትዮጵያ መንግስት የሚቃወሙ ድረ-ገጾች በሙሉ ታግደዋል። «ባለፉት ስድስት ዓመታት 11 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበችው» ኢትዮጵያ፣ ከሰሃራ በታች ካሉ አገራት መካከል በዝቅተኛ የኢንተርኔት አገልግሎት ፍሰት በሁለተኝነት ደረጃ ላይ ትገኛለች።

ትልቅ ተቀባይነት ያለውና የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች የሆነው «ሲ.ፒ.ጄ.» በኢትዮጵያ በነፃው ፕሬስ ላይ የሚፈፀመውን ትንኮሳና ያልተገባ አያያዝ በተደጋጋሚ አውግዞታል። «ሲ.ፒ.ጄ.» በ2006 ባወጣው ሪፖርት፣ ኢትዮጵያ «ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ በፕሬስ ነፃነት እጅግ አስከፊ በሆነ አኳሃን የኋልዮሽ በመንገዝ ላይ ያለች አገር» መሆኗን አስታውቆ ነበር። የአሜሪካ የውጭ ጉዳዮች መስሪያ ቤት /«ስቴት ዲፓርትመንት»/ በ2008 ባወጣው ሪፖርት፣ «መንግስት ጋዜጠኞችን፣ አሳታሚዎችንና አዘጋጆችን ማሰሩን፣ መተንኮሱንና መክሰሱን ገፍቶበታል። ከሶስት የ«ኤፍ.ኤም.» ሬዲዮ ጣቢያዎች በስተቀር ሁሉንም የኤሌክትሮኒክስ ማዲያዎች በመንግስት ቁጥጥሩ ስር ናቸው ያሉት። የግልና የመንግስት ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ ራሳቸውን ሳንሱር ያደርጋሉ» በማለት ገልጾ ነበር። በ2009 ደግሞ፣ ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች ተሟጋች ቡድን ባወጣው ሪፖርት፣ ኢትዮጵያ በፕሬስ ነፃነት ሰንጠረዥ (ደረጃ) ከ175 አገራት ውስጥ 140ኛ ደረጃን እንዳገኘች ገልጾ ነበር (ዚምባቡዌ ከ175 አገራት 136ኛ ደረጃን አግኝታለች)።

እንደመንግስት አቋም ከሆነ «በኢትዮጵያ ውስጥ የፕሬስ ነፃነት እየተጠናከረ የሄደ ነው፤ የሲፒጄ ሪፖርቶች «እውነታውን» የሚያንጸባርቁ አይደሉም። እንደ አቶ መለስ፣ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ነው። ማንም ሰው መንግስትን መተቸት እንደሚችልና «ሲ.ፒ.ጄ.» እና ሌሎች በርካታ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶችና የፕሬስ ተሟጋች ደርጅቶች የሚያቀርቧቸው ውንጀላዎች የፈጠራ ናቸው። እንዲህ በማለት ያብራል:- «መንግስትን መተቸት ወይም ፖሊሲዎቹን አለመቀበል ወይም የተለየ አመለካከታቸውን በፈለጉት መንገድ መግለጽን በተመለከተ አንዳች የመረበሽ ስሜት አላቸው ብዬ አላስብም። . . . የአገር ውስጥ ጋዜጦችን አንብበሀል? ስለመንግስት ሲናገሩ አንዳች ቃላት ያጥራቸዋል? . . .።»

ባለፈው ዓመት፣ የፕሬስ ሕግ በሚል፣ ነፃውን ፕሬስ ወንጀለኛ የሚያደርግ አምባገነናዊ አዋጅ ጸድቋል፤ «ማንኛው ሰው የሽብር ተግባሮችን የሚያበረታታ . . . ማንኛውንም የማስተዋወቅ መልዕክት የፃፈ፣ ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ ያሳተመ፣ ይፋ ያደረገ፣ ያሰራጨ፣ ያሳየ፣ እንዲደመጥ ያደረገ ከአስር እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።» በይስሙላ ፍርድ ቤቶች ለተከሰሱ ጋዜጠኞች ለእነርሱ «የሽብር ተግባር» ምን ማለት እንደሚሆን እስኪ ይገምቱት። ሕጉ ከመጽደቁ በፊት «ሂውማን ራይትስ

ዎች» ረቂቁን ተቃውሞት ነበር፤ «የኢትዮጵያ የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ፖለቲካዊ ንግግሮችንና ሰላማዊ ተቃውሞዎችን እንደሽብር ተግባር የሚያስቀጣ ሊሆን ይችላል፤ ከፀደቀም የተዛባ ፍርድን ያበረታታል፡፡» የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ መሪ የሆኑት አቶ ቡልቻ ደመቅሳም አስፈሪው ሕግ የሚፀድቅበት ቀን አስፈሪ ሆኖ ይኖራል በማለት «ይህ ሕግ የፀደቀበትን ቀን በኢትዮጵያ የታሪክ ጥራዝ ውስጥ ጨለማው ቀን አድርጌ ነው የምወስደው፡፡» ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በግንቦት 2009፣ «ከ101 በላይ ጋዜጠኞች ከአገር ለመሰደድ መገደዳቸውንና አስራ አንዱ ደግሞ አሁን ድረስ በኬንያ፣ ዩጋንዳ፣ የመን፣ ጃፓንና ሕንድ በከፍተኛ እንግልት ላይ ይገኛሉ፡፡» በማለት የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማሕበር ሪፖርት አድርጓል፡፡ ማሕበሩ በቅርቡ የተከሰቱ ክንውኖችን በትክክልና በግልጽ ተመልክቶት የገመተው ሪፖርት ነበር፤ «ጋዜጠኞች ሰርካለም ፋሲል፣ እስክንድር ነጋና ሲሳይ አጌና አሁን ድረስ የፕሬስ ፈቃድ የማግኘት መብት ተነፍገዋል፡፡ የአውራምባ ታይምስ፣ የሐራምቤ፣ የዕንቁና የአዲስ ነገር ሳምንታዊ ጋዜጦች አዘጋጆች በገኘው ግንባር ላይ የሚሰነዘር ማንኛውንም ትችት ዝም ማሰኛነት መሳሪያ በሆነው በአዲሱ የፕሬስ ሕግ ተደጋጋሚ ማስፈራሪያ እየተንገላቱ ነው፡፡»

በኢትዮጵያ ውስጥ በገለልተኛ ፕሬሶች ላይ የተከፈተው ጦርነት ከሚነገሩ መደነቅ ከሚገባቸው አስገራሚ ንግግሮች ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ አምባገነኑ አገዛዝ ነፃውን ፕሬስ ለማውደም የሚጠቀማቸው እጅግ ግዙፍ የጦር መሳሪያዎች አሉት፤ ጋዜጠኞች፣ አሳታሚዎችና አዘጋጆች አገር ለቀው እንዲወጡ ማስገደድ፤ እምቢተኞችን የገንዘብና የኢኮኖሚ አቅማቸውን ማንኮታኮት፤ በገለልተኛ ጋዜጠኝነት ለመሰማራት ሕጋዊ ፍቃድ ለማግኘት ለሚፈልጉ ፍቃድ መከልከል፣ ማዘግየትና አለማበረታታት፤ ካለምህረት ጋዜጠኞችን ለማደን፣ ለመተንኮስ፣ ለመመርመርና ለማስፈራራት የፖሊስንና የደህንነት ኃይሎችን መጠቀም፤ በከንቱ የጋኔንነት ገጽታ ለመስጠት በሚያደርገው ሙከራ ገለልተኛ ጋዜጦችን እና አዘጋጆችን በሬዲዮና በቴሌቪዥን የስም ማጥፋት እና የማዋረድ ዘመቻዎችን ማድረግ፤ ሕዝብ ከገለልተኛ ፕሬስ መረጃ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ እና ሰብዓዊ መብቱን ለማስጠበቅ የሚሰነዘርባቸው ጥቃት ያልበገራቸውን ለመወንጀል ያረጁና አዳዲስ የፈጠራ የወንጀል ክሶችን ማንቀሳቀስ፤ እና በታማኝነት መረጃን ለሕዝብ ለማቅረብ የግንባሩን መስመር ለመከተል ፍቃደኛ ያልሆኑ የራሱን ሪፖርተሮች እና ጋዜጠኞችን ማሰር፡፡

ይህንን ከፍተኛና ጨፍላቂ ኃይል ተቋቁመው የሚሰሩ በእጃቸው ከእርሳስ፣ ከብዕርና ከኮምፒውተር «ኪቦርድ» በስተቀር ምንም ያልያዙ በነፃነትና በሰብዓዊ መብቶች ሙሉ እምነትና ተስፋ በልባቸው የሰነቁ ጥቂት ቆራጥና ጀግና ጋዜጠኞች አሉ፡፡ እርግጥ ነው አምባገነኑ ያወጀውን ጦርነት እያሸነፈ ነው፡፡ ወጣትና እጅግ ብሩህ ጋዜጠኞች አገር

ለቀው እየተሰደዱ ነው። ሌሎች ደግሞ ሌላኛውን ወርጅብኝ እየተጠባበቁ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ነፃ ፕሬስ ሙሉ በሙሉ ድባቅ ለመምታትና ዝም ለማሰኘት የተከፈተው የተቀናጀ ዘመቻ ሙሉ በሙሉ ፊር ይዟል። አገዛዙ ገለልተኛ ጋዜጦችን አንድ በአንድ አሽመድምዷል፤ አዘጋጆቹንና ጋዜጠኞቹን አስወግዷቸዋል ወይም አስሯቸዋል። አሁን ደግሞ *አውራምባ ታይምስን* ለመዝጋት ዘመቻው ተጧጡፏል። የአምባገነኑ ጋዜጦች የአውራምባ ታይምስ አዘጋጆችንና ጋዜጠኞችን መልካም ስም ለማጠልሸትና ለማቆሸሽ በተቀናጀ አካሄድ እየፃፉባቸው ይገኛሉ። ላለፉት ጥቂት ዓመታት የአውራምባ ታይምስ ባልደረቦች ተከታታይ ማስፈራራት፣ እስርና ማስጠንቀቂያዎች ደርሷቸዋል።

በተጨማሪ፣ አምባገነኑ ድል የነሳበትን ጦርነት በሰርካለም ፋሲልና በባለቤቷ እስክንድር ነጋ ላይ ከፍቷል። ሰርካለም በ2007 በስርዓቱ ወሂኒ ቤት ልጇን ለመውለድ ተገዳ ነበር። በተከታዩ ዓመት «Counage in Journalism Award» የተሰኘ ትልቅ ሽልማት ከዓለም አቀፍ የሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን ተቀብላለች። ፋውንዴሽኑ ባወጣው መግለጫ፣ «ሰርካለም የታሰረችው በ1997 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫዎች የመንግስትን አካሄድ የተቹ ጽሁፎች በማሳተሟ ነበር። ነፍሰ ጡር የነበረችው ሰርካለም፣ በታረችበት ዕለት በፖሊስ በእጀጉ ድብደባ ደርሶባት ነበር።» ምንም እንኳን ሰርካለምና እስክንድር ከተመሰረተባቸው ክስ ነፃ ተደርገው «ይቅርታ» ተቀብለው የነበረ ቢሆንም አምባገነኑ አገዛዝ ባለፈው ሳምንት ባቀረበው «ይግባኝ» ንብረታቸውን በመውረስና እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ የገንዘብ አቅማቸውን በማንኮታኮት ጋዜጠኞቹን ከነጭራሹ የማጥፋት እቅዱን ግልጽ አድርጓል።

የአዲስ ነገር ጋዜጠኞች «አካላዊ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ» አገራቸውን ለቀው በመውጣት «እጅግ አስቸጋሪና ልብ ሰባሪ ውሳኔያቸውን» ለማድረግ ተገደዋል። ህይወታቸውን ለማዳን ማምለጥ ነበረባቸው፤ እንዳሉት ውሳኔያቸው «በአዲስ ነገር ላይ የኢትዮጵያ መንግስት የወራት ማሳደድ፣ ማስፈራራትና እልም ያለ ፕሮፓጋንዳ መደምደሚያ ነው።» በአዲሱ አምባገነናዊ የጸረ-ሽብርተኝነት ሕግ መሰረት «ሽብርተኛ ድርጅቶችንና የድርጅቶቹን አመለካከቶች ማስተዋወቅ»ን ጨምሮ ሌሎች የወንጀል ክሶች በቅርብ ሊመሰረትባቸው እንደነበር ጥቆማ ደርሷቸዋል። በቀጣይ ደወሉ የሚደወለው ለማን ነው - ለአውራምባ ታይምስ?

የአዲስ ነገር አዘጋጆችና ሪፖርተሮች በኢትዮጵያ ውስጥ የበሰለና አመክንዮ የተላበሰ ፖለቲካዊ ውይይት እና የሀሳብ ልውውጥ እንዲጐለብት ሳምንታዊዋን ጋዜጣ ማሳተም ከጀመሩበት ዓመት አንስቶ ለእውነት ክብርና ጀግንነት የተላበሰ ትግል አውጀው የነበረ ሲሆን ጋዜጠኞቹ የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ተሚጋጮች አዲስ ትውልድ ናቸው። ጋዜጣው በነፃው ፕሬስ ላይ የታወጀውን ጦርነት ቢሸነፍም የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብና

አእምሮ በቀላሉ ለማሸነፍ ከተቻላቸው ጥቂት አይበገሬና ኩሩ ኢትዮጵያውያን መካከል የሚጠቀስና ተጠናክሮ ለመስፋፋት የቻለ ነበር፡፡ «በስርጭት፣ ተጽዕኖ በማሳደርና በኢንቨስትመንት እጅግ አስደናቂ እድገት» አግኝቷል፤ በአምባገነንነት ድብን ያለ ጨለማ ውስጥ በመስራት፣ በሳምንት 30 ሺህ ኮፒ ለአንባቢ ለማቅረብ መቻል እጅግ በጣም የተለየ ስኬት ነው፡፡ በሚዛናዊነቷ፣ በጋዜጠኝነት ድፍረቷና በምታነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች ስፋት አዲስ ነገር አድናቆትን ተቀዳጅታለች፡፡

በአዲስ ነገር የመጨረሻ ምዕራፍ በተሰጠ መግለጫ አዘጋጆቹ ከዚህ ቀደም በርካቶች የጠየቁትን ጥያቄ ፍንትው ባለ አገላለጽ ጠይቀው ነበር፤ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፍጨረጨሩ የሚገኙ ጥቂት ገለልተኛ የግል ጋዜጦችን ለመደፍጠጥ ስለምን መንግስት ቁምስቅሉን ያያል? ምላሹ ቀላል ነው! አምባገነኖች ከምንም በላይ እውነትን ይፈራሉ! ገለልተኛ ሚዲያዎች፣ አምባገነኖች በየቀኑ የሚፈጽሟቸውን ወንጀሎችና ኢ-ፍትሃዊ ተግባሮች የሚያንፀባርቁ ማጉያ መስታወቶች ናቸው! አምባገነኖች እያንዳንዷን ቀን የሚያሳልፉትና የሚኖሩት በሂሲና ወቀሳ በመሆኑ ትችትና እውነተኛ የሕዝብ አስተያየቶችን ይፈራሉ፡፡ በፈጸሟቸው ወንጀሎች እንጠየቃለን በሚል ፍራቻ ሌሊቱን እንቅልፍ በዓይናቸው ሳይዞር ያነጉታል፡፡ አምባገነኖች ልክ የባህር ማዕበል አንድ ነጠላ ውርጅብኝ ሲያርፍበት ወዲያው እንደሚሟሟ በአሸዋ ላይ እንደተገነባ ቡት ናቸው፡፡ አምባገነኖች በጠንካራ የሕዝብ ቁጣ ማዕበል በታሪክ የቆሻሻ ማከማቻ ቅርጫት እንወረወራለን በሚል ፍራቻ ምክንያት ገለልተኛ ፕሬስን ማንኮታኮትና ሕዝብን ማሸበር ግድ ይላቸዋል፡፡

አምባገነኖች በገለልተኛ ፕሬስ ስለምን ይሸበራሉ? ለሚለው ሌላም ምክንያት አለ፡፡ አምባገነናዊ መንግስታት ልክ እውነትን እንደሚፈሩት ሁሉ ወጣቱን ይፈራሉ፡፡ ነፃው ፕሬስ ወጣቱን የመሳብ ጉልበት አለውና አይናቸውን በመግለጥ አእምሮአቸውን ንቁና ነቃሽ አድርጎ ያንፃል፡፡ አዲስ ነገር በርካታ ደጋፊዎች እንደነበሯት ምስጢር አይደለም፡፡ በወጣቱ እጅግ የሚቀነቀኑ እሴቶች - ነፃነት፣ ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች - የውይይት መድረክ ነበረች፡፡ በሙሉ አቅሙ የሚንቀሳቀስ ገለልተኛ ፕሬስ እያለ ወጣቱን በጨለማ መሸበብ አይቻልም፡፡ የአዲስ ነገር ጋዜጠኞችን፣ ጋዜጠኛ ሰርካለምንና እስክንድርንና ሌሎች ጋዜጠኞችን ይመልከቷቸውማ፡፡ ሁሉም በአገራቸው፣ በሕዝባቸውና በነፃነት የሚያምኑ ናቸው፡፡ ያ የአምባገነኖችን የልብ ትርታና ምት ጸጥ አድርጎ በልብ ድካም የሚወስዳቸው አስፈሪ እውነት ነው፡፡

የገለልተኛው ፕሬስ ፍልሚያ ከነአካቴው በሽንፈት አልተቋጨም፡፡ ኢትዮጵያን እየሸበባት ባለው ጨለማ ላይ የሚፈነጥቅ የብርሃን ጮራ የሚረጩ የውጪ አገር ጋዜጠኞች በአገሪቱ ይገኛሉ፡፡ ሬውተርስ፣ አሶስየትድ ፕሬስ፣ ኒው ዮርክ ታይምስ፣ ብሉምበርግ፣ ቢቢሲ፣ ቪኦኤና ሌሎች በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአይን እማኞች

ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጭ ሚዲያ በሪፖርተርነት መስራት በጭራሽ ቀላል አይደለም። በተዘዋዋሪ መጠነኛ ማስፈራሪያ፣ ትንኮሳና ዛቻ ለእነርሱም ይደርሳል። በ2006፣ «የአገሪቱን ገጽታ አጠልሽቷል» በሚል ውንጀላ የአሶስየትድ ፕሬስ ሪፖርተር ከአገር እንዲወጣ ተደነ ነበር። እነዚህ የውጭ ሚዲያ ጋዜጠኞች በሚያቀርቧቸው ሪፖርት ሚዛናዊነትን በመጠበቃቸው፣ ወገንተኛነትን በማስወገዳቸውና ትክክለኛውን መረጃ በማስተላለፋቸው ሊመሰገኑ ይገባል። የተመለከቱትን ሳይጨምሩ ሳይቀንሱ ይዘግባሉ ምክንያቱም የጋዜጠኝነት ሙያና ሥነ-ምግባር እንደዚያ ያዛቸዋልና ነው። በሪፖርታቸው ልንስማማ ወይም ላንስማማ እንችላለን። ሆኖም ለአሁኑ ያሉን እነርሱ ብቻ ናቸው።

ይህ እንግዲህ በኢትዮጵያ በገለልተኛው ፕሬስ ላይ የታወጀው ያልተቋጨ ስልታዊ ጥቃት ታሪክ ነው። በመጨረሻ፣ ጉራዴ በታጠቁ አምባገነኖችና ጦማር ብቻ ባነገቱ ጋዜጠኞች መካከል እየተካሄደ ያለው ፍልሚያ የሚደመደመው በኢትዮጵያ ሕዝብ ልብና አእምሮ ውሳኔ ብቻ ነው።

መሰረታዊው ጥያቄ፣ መንግስትን መታደግ ወይንስ ነፃውን ፕሬስ? የሚል ከሆነ ልክ እንደ ቶማስ ጀፈርሰን የመጨረሻውን እመርጣለሁ፡-

> የመንግስታችን መሰረት የሕዝብ አስተያየት ነውና፣ ከሁሉም ቀዳሚው አላማ የሚሆነው ያን መብት ማስጠበቅ ነው፤ እና ጋዜጦች ከሌሉበት መንግስትና መንግስት የሌለበት ግን ጋዜጦች ካለቡት ሥርዓት መካከል ምረጥ ብባል፣ የመጨረሻውን ለመምረጥ አላንገራግርም።

ታምራት ነገራ፣ አብይ ተ/ማርያም፣ ግርማ ተስፋ፣ ማስረሻ ማሞ፣ መስፍን ነጋሽ፣ ዘሪሁን ተስፋዬ፣ አብርሃም በጊዜው፣ ሰርካለም ፋሲል፣ እስክንድር ነጋ እና ሌሎች የኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት ተከላካዮች፣ ለዘለዓለም ልናሰግናችሁ እዳ አለብን!

**/አለማየሁ ገብረማሪያም፣በካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ፣ ሰንበርናንዲኖ የፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰርና የህግ ባለሙያ ሲሆኑ የአለማችን ታዋቂ ሰዎችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ሀሳባቸውን የሚያንሸራሽሩበት «ሃፊንግተን ፖስት» ቋሚ ጸሐፊ ናቸው/**